# ኣትራፊ - ቀጣፊ!

እንዲህም ተብሎ፣ እንደዚያም ተብሎ
ጥቀርሻን ሸፋፍኖ በጥጥ ኣመልማሎ
በወረቀት መሳይ፣ በሻሽም ጠቅልሎ
ማሳሳት፣ ማታለል፣ በሓሰት ሸንግሎ
ገደል ውስጥ  መክተት  ነው ሰውን ኣባብሎ…
        በፍጹም ኣይደንቅም የቆየ ነውና
        ኣዲስ ኣላየንም፣ ምንስ ሓቅ ኣለና?
እንዲህም ተብሎ፣ እንደዚያም ተብሎ
ጥቀርሻን ሸፋፍኖ ወርቅም ኣስመስሎ
        በዓለም ላይ  የሚገኝ ትርፍ የሚባል ሁሉ
        በማታለልና ማጭበርበር ነው ኣሉ።

ገ/ኢ. ጐርፉ።